# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)


## ልዩ መግለጫ:
## ቅንጅትን ለማጥፋት የሚደረገው ሴራ ይከሽፋል!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን አገዛዝ በአገራችን በኢትዮጵያ ለሕዝብና ለብሔራዊ ጥቅም የቆሙ እውነተኛና ሃቀኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ የሚያደርገውን ቀጣይ ዘመቻ አጥብቆ ያወግዛል።

የአቶ መለስ ዜናዊ ኢሕአዴግ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች በሆኑት የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) እና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዴኅ) ላይ ቀደም ሲል የወሰደውን ለማፍረስና የኢሕአዴግ ትእዛዝ ፈፃሚና ተላላኪ በሆኑ ምልምሎችና አንዳንድ የዋሃን የተሞሉ ቡድኖችን በስማቸው ለመፍጠር እንደሞከረው ሁሉ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛውን ድምፅ አምኖ የሰጠውንና መሪዎቹ በግፍና በሕገ-ወጥ መንገድ በእስር የሚገኙትን ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት) ፓርቲን እንደለመደው ጠፍጥፎ በመሥራት አሻንጉሊት "ቅንጅት" ፈጥሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲቀበል ለማድረግ እየኳተነ ይገኛል።

መቸም ሃፍረትና ይሉኝታ የማያውቀው የአቶ መለስ አሸባሪ ቡድን ለሕዝብ ያለው ንቀት ለከት የለውምና የሕዝብን ድምፅ ሰርቆና ሁለንተናዊ መብቱን እረግጦ ሲያመቸው በሽንገላ አለበለዚያም በለየለት አረመኔአዊ የግፍ እርምጃ በጉልበት ለመግዛት መወሰኑና እንደዚህ ዓይነቱን ተራ ማጭበርበር ድምፁን የተቀማና የመረጣቸው ወኪሎቹ የታሰሩበት ኩሩውና ቆራጡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀላሉ ይቀበላል ብሎ ማሰቡ ግብዝነቱን ብቻ ነው የሚያረጋግጠው።

ዴሞክራሲያዊና በሕዝብ ዘንድ አመኔታና የተሻለ ተቀባይነት ያላቸውን ድርጅቶች በማፍረሱ ጨዋታና ደባ ውስጥ ከማንኛውም መደበኛ ዲፕሎማሲያዊ ምግባርና ሃላፊነት በማይጠበቅ ሁኔታ አንዳንድ የውጭ አገር ተወካዮች በሚያደርጉት የአጉል ማጋፈር ተግባር ኅብረቱ እጅጉን አዝኗል። እነኝህ ክፍሎች አሸባሪውን የአቶ መለስ አምባ-ገነን አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ እንደተፋው ቢረዱም ይኸ ቡድን ተነጥሎ ራቁቱን ቆሞ ዴሞክራሲ አለ ማለት ስለማይቻላቸው፥ ይኸም ለሱ የሚያደርጉትን ድጋፍ ለመቀጠል አስቸጋሪ ስለሆነባቸው በተቃዋሚው ስም ስስ ጎንና ልል አመለካከት እንዲሁም ዘንቦ ተባርቆ ሥልጣን ጠብ ብትል ብለው አንጋጠው የሚያዩ ሃፍረተ ቢስ ግብዝ ወዶ-አደሮችን በተቃዋሚው ስም በአጃቢነት ለማሰለፍ የአቶ መለስ ቡድን በሚያደርገው ጥረት መተባበራቸውና አልፎም አስተናባሪ መሆናቸው መታየት ከጀመረ ውሎ አድሯል።

እውን እነኝህ ተቃዋሚ ነን ባዮች በተቃዋሚው ስም በኢሕአዴግ የሌቦች ዋሻ ፓርላማ ውስጥ ኢሕአዴጋዊ የአጃቢነት አገልግሎታቸውን በታማኝነት ባይሰጡና ባይተባበሩ የሕዝቡ ትግል ምን መልክ ይይዝ ነበር? አንዳንድ የውጭ መንግሥታትስ ኢሕአዴግን ለመደገፍ በቂ ምክንያት ይኖራቸው ነበር? ይደፍሩስ ነበር? እነሱስ ለኢሕአዴግ ሽፋን ከመሆንና እሱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጽመውን ወንጀል ከመጋራት ውጭ ምን ፈየዱ? ለመሆኑ ነገ እንደሚያስጠይቃቸው ያውቁታል?


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም የማይጨነቀው ኢሕአዴግም ሆነ ከራሳቸው በጣም ጠባብና የዞረበት ጊዜአዊ ጥቅም ብቻ በመነሳት እሱን ለመርዳት ሰበብና ሽፋን የሚፈልጉ አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ቀደም ሲል በወዶ-ገብነት የኢሕአዴግ ታማኝ አገልጋይ ሆነው የተሰለፉ ክፍሎች ያስገኙትን ጊዜኣዊ የሽፋን ጠቀሜታ ስለተገነዘቡ ቅንጅቱን ጨርሶ እንደሌለ ለመቁጠርም ሆነ ጨርሶ ለማጥፋት የነበራቸውን ህልም ትተው በአፍርሶ መጠፍጠፉ አማራጭ ላይ ቆርጠው ተሰልፈዋል፡፡ ይሁንናም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደዚህ ዓይነቱን እኩይ ተግባርና አጉል ትርኢት በንቀት ከማየትና ተባባሪ ሽር ጉድ ባዮችን በሃዘኔታና በትዝብት ከመመልከት በስተቀር በምንም መንገድ ሊቀበለው አይችልም፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ይኸንን መሰሪኣዊ ተግባር አምርሮ እየኮነነ በዚህ ቅንጅትን ለማፍረስና በስሙ ጉልት ለማስቀመጥ በሚደረግ ተውኔት ማንም በጎ አሳቢና አገር-ወዳድ ዜጋ እንዳይተባበር እየጠየቀ፥ በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩ ወገኖችም የቅርቡ ሳይሆን የዘለቄታው፥ የግሉ ሳይሆን የጋራውና ሕዝባዊው ዓላማ ታይቷቸው ከእንደዚህ ዓይነት በታሪክ አስወቃሽ፥ እሳፋሪና አስጠያቂ ተግባር እራሳቸውን እንዲቆጥቡ አጥብቆ ያሳስባል፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም